መልእክት አራት

**በእግዚአብሔር ነቢያት**
**መለኮታዊ ማበረታታት በኩል**
**የእግዚአብሔር ቤት ግንባታ ምለሳ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:- ዕዝ. 5፡1-2፤ ሐጌ 1፡2-5፣ 7-8፣ 9፣ 14፤
2፡6-7፣ 9፣ 23፤ ዘካ. 3፡9፤ 4፡2-7፣ 11-14

I. **የተመለሰው መቅደስ እንደ እግዚአብሔር ቤት መልሶ ሲገነባ፣ ኢያሱም (ክህንነትን በመወከል) ዘሩባቤልም (ንግሥናን በመወከል) ሁለቱም ደካማ እና ተስፋ የቆረጡ ሆኑ፤ ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ኢያሱን እና ዘሩባቤልን ለማጠንከር፣ ለማገዝ እና ለማበረታታት ነቢያቱ ሐጌን እና ዘካርያስን ለእርሱ እንዲናገሩለት ተጠቀመባቸው—ዕዝ. 5፡1-2፤ ተዛ. 1 ቆሮ. 14፡3።**

II. **የሐጌ ትንቢት ማዕከላዊ ሃሳብ የእግዚአብሔር ቤት፣ የእግዚአብሔር መቅደስ ግንባታ ዛሬ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ደህንነት ጋር እና በመታደስ ዘመን ከመሲሑ ጋር የሺህ ዓመቱ መንግሥት ከመምጣቱ ጋር የተገናኘ ነው—ሐጌ 1፡2-5፣ 7-8፣ 9፣ 14፤ 2፡6-9፣ 20-23፤ ማቴ. 19፡28፤ ሐዋ. 3፡20-21፡-**

ሀ. በብሉይ ኪዳን የያሕዌ ቤት ወይም መቅደሱ በመጀመሪያ ተናጠል በሆነ መልኩ እንደ እግዚአብሔር ቤት የክርስቶስ ምሳሌ ነበር፣ ከዚያም ብዙዎች በተካተቱበት መልኩ እንደ እግዚአብሔር ቤት የቤተ ክርስቲያን፣ የአካሉ፣ የተለቀው ክርስቶስ ምሳሌ ነበር—ዮሐ. 2፡19-21፤ 1 ጢሞ. 3፡15።

ለ. የያሕዌ ቤት የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ስለሆነ፣ እኛም የምሳሌው እውነታ ስለሆንን የሐጌ ትንቢት እኛን፣ የአዲስ ኪዳን አማኞችን ያመለክታል።

ሐ. ሐጌ ለገገርው ዘሩባቤል እና ለታላቁ ካህን ኢያሱ መናገሩ ለመቅደሱ እንደ እግዚአብሔር ቤት መልሶ መገንባት እነርሱን እና ሕዝቡን ለማጠንከር እና ለማበረታታት ነበር—ዕዝ. 5፡1፤ ሐጌ 1፡1።

መ. ራስን-አገልጋዮቹ እና እግዚአብሔርን-ቸል ባዮቹ የተመለሱ ምርኮኞች ለያሕዌ ቤት ሳይሆን ለራሳቸው ቤቶች ግድ ሲሰኙ ነበር (ቁ. 4)፤ ቁጥር 9 ላይ *አየሮጣችሁ* የሚለው ቃል ሕዝቡ ለራሳቸው ቤቶች ግድ በመሰኘት ተጠምደው እንደነበር ያመለክታል።

ሠ. ቤተ ክርስቲያንን ቸል ካልን፣ እውነተኛ ድሰታ ወይም እርካታ እንደማይኖረን ሐጌ 1፡6 ያመለክታል፤ የእግዚአብሔር ቤት ግንባታ ምለሳን በተመለከተ፣ ገለልተኛ መሆን አንችልም፤ በመጀመሪያ ለቤቶቻችን ግድ በመሰኘት ወይም መጀመሪያ ለጌታ ቤት ግድ በመሰኘት ፍጹም መሆን አለብን—ማቴ. 6፡33፤ ሉቃ. 9፡57-62፤ ፊልጵ. 2፡20-21።

ረ. ለእግዚአብሔር ቤት ግንባታ ምለሳ፣ የእግዚአብሔር ምርጦች በመንፈሳቸው ተነሳስተው መጡ፣ በያሕዌ ቤት ውስጥም ሥራ ሠሩ፤ ለጌታ ትእዛዝ በምንሰጠው ምላሽ፣ ለጌታ ቤት፣ እንደ ክርስቶስ አካል ለቤተ ክርስቲያን ግንባታ ወንጌልን በመስበክ፣ አዳዲስ አማኞችን በመመገብ እና ሌሎችን በመንከባከብ ሥራ ሁላችንም በጌታ ኢየሱስ የተሞላን መሆን አለብን—ሐጌ 1፡14፤ 2፡7፤ ዮሐ. 21፡15-17።

ሰ. "አሕዛብን ሁሉ አናውጣለሁ፥ በአሕዛብ ሁሉ የተመረጠውም ዕቃ ይመጣል"—ሐጌ 2፡7፡-

1. ይህ የአሕዛብ ሁሉ መሻት የሆነውን ክርስቶስን ያመለክታል፤ አሕዝብ ክርስቶስን ባያውቁትም እንኳን፣ ክርስቶስን ይሹታል፤ አሕዛብ እውነታው ክርስቶስ የሆነውን እንደ ብርሃን፣ ፍቅር፣ ደስታ እና ጽድቅ ያሉ ነገሮችን መሻታቸው፣ ሳይታወቃቸው ክርስቶስን ይሻሉ ማለት ነው—ሚል. 3፡1።
2. እንደ የአሕዛብ ሁሉ መሻት የክርስቶስ መምጣት የእግዚአብሔር ሕዝብ በባቢሎን ከተማረኩበት በመመለሳቸው እና በእግዚአብሔር ቤት ግንባታ ምለሳ ላይ ይመረኮዛል—1 ጢሞ. 3፡15፤ 1 ጴጥ. 2፡5።

ሸ. "ይህንም ቤት በክብር እሞላዋለሁ... ከፊተኛው ይልቅ የዚህ የሁለተኛው ቤት ክብር ይበልጣል"—ሐጌ 2፡7፣ 9፡-

1. የእግዚአብሔር ክብር፣ የእግዚአብሔር መገለጥ በእግዚአብሔር ግንባታ፣ በያሕዌ ቤት ውስጥ ነው—ዘጸ. 40፡34-35፤ 1 ነገ. 8፡10-11፤ 2 ዜና 3፡1፤ 5፡1-2፣ 13-14፤ ኤፌ. 3፡21፤ ራእ. 21፡10-11።
2. ሕዝቅኤል በእግዚአብሔር ራእይ የያሕዌ ክብር ወደ ያሕዌ ቤት ሲመለስና ቤቱን ሲሞላው አየ (ሕዝ. 43፡1-5)፤ የያሕዌ ክብር ወደ ቤቱ የተመለሰው የቤቱ ግንባታ ስለተጠናቀቀ ነበር (ቁ. 2፣ 5)፤ ይህ የሚያመለክተው የክብር አምላክ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲኖር፣ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መኖሪያ ስፍራ ለመሆን መገንባት እንዳለባት ነው (ኤፌ. 2፡21-22፤ 3፡14-21)።
3. ከእግዚአብሔር ቤት የሚፈሰው የሕይወት ውኃ ወንዝ ወደ ምሥራቅ፣ ወደ እግዚአብሔር ክብር አቅጣጫ መሆኑን አየ (ሕዝ. 47፡1፤ 43፡2)፤ ለእግዚአብሔር ክብር ግድ ካልተሰኘን፣ በውስጣችን ያለው ፍሰት ይገደባል።

4. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ግድ ልንሰኝለት የሚገባው የመጀመሪያው ነገር የጌታ ክብር ነው፤ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ያሉ ውሳኔዎች ከሁሉ አስቀድሞ በጌታ ክብር መሠረት መሆን አለባቸው—ኤፌ. 3፡21፤ 4፡20፤ 1ጴጥ. 4፡10-11፤ ይሁ. 24-25።
5. የእግዚአብሔር መክበር የአገልግሎታችን ዓላማ ነው፤ ለእግዚአብሔር መስጠት የምንችለው ከፍተኛው አገልግሎት የአምላክ-ሰው ሕይወት በመኖር እግዚአብሔርን ማክበራችን ነው (ኢሳ. 43፡7፤ ዮሐ. 7፡16-18፤ 17፡1-4፤ ሮሜ 9፡21፣ 23፤ ፊልጵ. 1፡19-21፤ 1 ቆሮ. 6፡19-20፤ 10፡31)፤ ይህ እግዚአብሔርን በጋራ፣ በተገነባ መንገድ እንድንገልጠው እና በመለኮታዊው ክብር ውስጥ ወዳለው አንድነት ውስጥ እንድንገባ ነው (ዮሐ. 17፡22-24)።

ቀ. ያሕዌ ዘሩባቤልን እንደ ቀለበት ማተሚያ ማድረጉ (ሐጌ 2፡23) ያሕዌ እንደ ወኪሉ እንደቆጠረውና እንደወደደው፣ እንዳመነውም ያመለክታል፤ በዚህ ጉዳይ ዘሩባቤል የክርስቶስ ምሳሌ ነው፣ እርሱም እግዚአብሔር የሚወደውና የሚያምነው ነው (ማቴ. 3፡17፤ 17፡5፤ ዮሐ. 3፡35፤ 17፡2)፤ እንዲህ እንዳለው ማንነት፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ቤት፣ የቤተ ክርስቲያንን ግንባታ ለማከናወን ብቁ ነው (ማቴ. 16፡18)።

**III. እንደ ሰባቱ የያሕዌ ዓይኖች (ዘካ. 4፡10)፣ እንደ ሰባቱ የሚቤዠው በግ ዓይኖች (ራእ. 5፡6) እና እንደ ሰባቱ የግንባታው ድንጋይ ዓይኖች (ዘካ. 3፡9) ለሥስታንዱ አምላክ ሙሉ መገለጥ እና ለእግዚአብሔር ቤት መልሶ መገንባት፣ የመቅረዙ ሰባት መብራቶች (4፡2፤ ራእ. 4፡5) ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት፣ ሰባት እጥፍ ያየለው መንፈስ (1፡4)መሆናቸውን የዘካርያስ መጽሐፍ ይገልጣል፡-**

ሀ. በዘካርያስ 3፡9 በኢያሱ ፊት የተቀመጠው ድንጋይ ለእግዚአብሔር ግንባታ እንደሆነው ድንጋይ ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል (መዝ. 118፡22፤ ማቴ. 21፡42)፤ ያሕዌ ድንጋዩን መቅረጹ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት፣ በእግዚአብሔር እንደተቀረጸ፣ እንደተቆረጠ ያመለክታል፤ ያሕዌ የምድሪቱን በደል በአንድ ቀን ማስወገዱ፣ እግዚአብሔር የሠራበት ክርስቶስ የእስራኤልን ምድር ኃጢአት በአንድ ቀን እንደሚያስወግድ ያመለክታል፤ በመስቀል ላይ ሞቱ፣ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት አስወግዷል (1 ጴጥ. 2፡24፤ ዮሐ. 1፡29)፡-

1. ድንጋዩ፣ ያሕዌ እና በጉ አንድ ናቸው፤ ክርስቶስ የሚቤዠው በግ እና የግንባታው ድንጋይ ነው፣ እርሱ ያሕዌም ጭምር ነው፤ ክርስቶስ በጉ-ድንጋይ ነው—በጉ ለቤዛነት እና ድንጋዩ ለግንባታ—ራእ. 5፡6፤ ዘካ. 3፡9።
2. በእግዚአብሔር ግንባታ ውስጥ ክርስቶስ ግንባታውን አጽንቶ ለማቆም የመሠረቱ ድንጋይ፣ የአካሉ ብልቶች የሆኑትን አሕዛብን እና አይሁድን በአንድ ላይ ለማጋጠም የማዕዘኑ ድንጋይ፣ በእግዚአብሔር ግንባታ ውስጥ ሁሉንም ነገር ለማጠናቀቅ የሞገስ መደምደሚያ ድንጋይ ነው—ኢሳ. 28፡16፤ 1 ቆሮ. 3፡11፤ ኤፌ. 2፡20፤ 1 ጴጥ. 2፡6፤ ዘካ. 4፡7።
3. ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር በግ፣ ሰባት ዓይኖች ያሉት የግንባታው ድንጋይ የመሆኑ ሐቅ ሰባቱ የክርስቶስ ዓይኖች ለእግዚአብሔር ግንባታ መሆናቸውን ይገልጣል—ዮሐ. 1፡29፤ ዘካ. 3፡9፤ ራእ. 5፡6።
4. ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ግንባታ ወደ ከበሩ ዕቃዎች እኛን ለመለወጥ ራሱን ወደ ውስጣችን ለማስተላለፍ ሰባት ዓይኖች፣ ሰባቱ መናፍስት፣ ያሉት የግንባታው ድንጋይ ነው፤ ጌታ ሲመለከተን፣ ሰባቱ ዓይኖቹ ራሱን ወደ ውስጣችን ያስተላልፋሉ—ዘካ. 3፡9፤ 1 ቆሮ. 3፡12፤ ራእ. 3፡1፤ 5፡6።

ለ. ለእግዚአብሔር ግንባታ መጠናቀቅ፣ ሰባት እጥፍ ያየለው መንፈስ ለእግዚአብሔር ግንባታ እኛን ለመመልከት እና ለመመርመር፣ በክርስቶስ ውስጠ-ነገር፣ ብልጥግናዎች እና ሸክም ለመሰረጽ እና ወደ ውስጣችን ለማስተላለፍ እንደሚቤዠው በግ እና እንደ ግንባታው ድንጋይ የክርስቶስ ዓይኖች ነው—ዘካ. 3፡9፤ 4፡7፤ ራእ. 1፡14፤ 5፡6፡-

1. ሰባቱ የበጉ ዓይኖች እንደ ፍትሃዊው ተቤዢ በክርስቶስ ይሰርጹናል፣ ሰባቱ የድንጋዩ ዓይኖች ለግንባታው ግብ በፍትሃዊ ቤዛነቱ እና በሕይወታዊ ማዳኑ በኩል በምድር ላይ ላለው ለእግዚአብሔር ገቢራዊ እንቅስቃሴ በክርስቶስ እንደ ሕይወታዊው አዳኝ ይሰርጹናል—ዮሐ. 1፡29፤ ሐዋ. 4፡11-12፤ ሮሜ 5፡10።
2. በውስጣችን ሁለት መብራቶች አሉን—ሰባት እጥፍ ያየለው መንፈስ በመንፈሳችን ውስጥ (ምሳ. 20፡27፤ ራእ. 4፡5፤ 1 ቆሮ. 6፡17)፤ ለመለወጥ፣ ሰባት የእሳት መብራቶች ያሉት የጌታ መብራት የነፍሳችንን ጉርጆች ሁሉ እንዲመረምር፣ ለውስጥ ክፍሎቻችንን የሕይወት አቅርቦት ለመስጠት እንዲያበራባቸው እና አብርሆት እንዲሰጣቸው በጸሎት ለጌታ ሙሉ በሙሉ መከፈት አለብን።
3. ትልቅ መጠን ያለው መለወጥን የሚለማመድ ሰው ሙሉ በሙሉ ለጌታ የተከፈተ ሰው ነው፤ በክርስቶስ ፈላጊዎች ውስጥ ሰባት እጥፍ ባየለው መንፈስ አሠራር፣ የክርስቶስ ፈላጊዎች በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቀውን የክርስቶስን አካል ለመገንባት ድል ነሺዎች ለመሆን ያይላሉ።

ሐ. ክርስቶስ በትንሣኤው፣ እንደ ኋለኛው አዳም፣ ሕይወት-የሚሰጥ መንፈስ ሆነ (15፥45፤ ዮሐ. 6፥63፤ 2 ቆሮ. 3፥6)፣ እርሱ ሰባት እጥፍ ያየለው መንፈስም ጭምር ነው፤ ይህ መንፈስ የሕይወት መንፈስ ነው (ሮሜ 8፥2)፤ ስለዚህ፣ የሰባቱ መናፍስት ሥራ ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ መኖሪያ፣ ለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መገንባት ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ መለኮታዊውን ሕይወት ማስተላለፍ ነው።

መ. ሰባት እጥፍ ያየለው መንፈስ ለእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ መፈጸም ወርቃማዎቹን መቅረዞች ለማፍራት ለማንደድ፣ አብርሆት ለመስጠት፣ ለማጋለጥ፣ ለመመርመር፣ ለመፍረድ፣ ለማንጻት እና ለማንጠር ሰባቱ የእሳት መብራቶች ነው—ራእ. 4፥5፤ 1፥2፣ 4፣ 9-12፣ 20።

ሠ. በመቅረዙ ሁለት ወገን ያሉት ሁለቱ የወይራ ዛፎች ለእግዚአብሔር መቅደስ መልሶ መገንባት በያሕዌ መንፈስ የተሞሉትን፣ ሁለቱ የዘይት ልጆች የነበሩትን ታላቁን ካህን ኢያሱን እና በዚያን ጊዜ ገዢ የነበረውን ዘሩባቤልን ያመለክታሉ—ዘካ. 4፥1-6፣ 11-14፦

1. በተጨማሪም ሁለቱ የዘይት ልጆች በአሁኑ ዘመን የመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመታት ተኩል ላይ ለእግዚአብሔር ሕዝብ—ለእስራኤላውያን እና በክርስቶስ ለሚያምኑት—መጠንከር በታላቁ መከራ ጊዜ የእግዚአብሔር ምስክሮች የሚሆኑትን ሁለቱን ምስክሮች፣ ሙሴን እና ኤልያስን በምሳሌ ያሳያሉ—ራእ. 11፥3-12፤ 12፥17።
2. በመርህ ደረጃ፣ በክርስቶስ የሚያምኑ አማኞች ለሚያበራ ምስክርነቱ፣ ለኢየሱስ ምስክር ወደ መቅረዙ መንፈስን ለማፍሰስ የትኩስ ዘይት ልጆች፣ በትኩሱ፣ በአሁኑ እና በተጠናቀቀው መንፈስ እንደ የደስታ ዘይት የተሞሉ መሆን አለባቸው—1፥12፣ 20፤ መዝ. 45፥7፤ 46፥4፤ 92፥10፤ ዮሐ. 7፥38፦
   - ሀ. ቤተ ክርስቲያን እንደ መቅረዝ በመለኮታዊ ባሕርይው እንደ እግዚአብሔር ዘይት ሰባት እጥፍ ካየለው መንፈስ ጋር የሦስታንዱ አምላክ ጠንካራ አካል መልበስ ናት።
   - ለ. ዘይቱ ራሱ ወርቅ ነው (ዘካ. 4፥12)፣ ማለትም ወርቁ እንደ ዘይት ይፈሳል፤ ወደ መቅረዙ ውስጥ በይበልጥ ዘይት ሲጨመር፣ የበለጠ ወርቅ ተጨምሯል ማለት ነው።
   - ሐ. ለወርቃማዋ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም መገንባት ንጹሕ ወርቃማ መቅረዝ መሆን እንችል ዘንድ ዕለት ዕለት ብዙ ወርቅ፣ በመለኮታዊ ባሕርይው ብዙ እግዚአብሔር ለማግኘት ዋጋ መክፈል ያስፈልገናል—2 ጴጥ. 1፥4፤ ራእ. 3፥18፤ 1፥20፤ 21፥18፤ ማቴ. 25፥8-9።
   - መ. ይህን ጉዳይ ዛሬ ልምምዳችን ላይ ስንተገብረው፣ ከእኛ ወደ ውጪ የሚፈሰው መንፈስ እግዚአብሔር እንደሆነ እናያለን፣ እግዚአብሔር ደግሞ ወርቅ ነው፤ ስለዚህ፣ ክርስቶስን ለሌሎች ስናገለግል፣ ዘይትን እንደ አቅርቦት ስንሰጣቸው፣ በእርግጥም እግዚአብሔርን እየሰጠናቸው ነው፤ እግዚአብሔር ከውስጣችን ወደ እነርሱ እየፈሰሰ ነው—ዘካ. 4፥12-14፤ ዮሐ. 7፥37-39፤ 2 ቆሮ. 3፥3፣ 6፣ 8።
   - ሠ. ሁላችንም እግዚአብሔርን ከራሳችን ወደ ሌሎች የምናፈስስ የወይራ ዛፎች መሆን አለብን፤ በዚህ መንገድ እግዚአብሔር የሚፈስስባቸው የወይራ ዛፎች በሆኑት አማካኝነት ዘይት ለሚያስፈልጋቸው ዘይት ይቀርባል—ሮሜ 11፥17፤ ሉቃ. 10፥34፤ ተዛ. ዮሐ. 7፥37-39።

© 2022 Living Stream Ministry